## ሄፓታይተስ ቢ ምንድን ነው?

ሄፓታይተስ ቢ በ ሄፓታይተስ ቢ ቫይረስ የሚከሰት አደገኛ የጉበት ኢንፌክሽን ነው። ለጥቂት ሳምንታት የሚቆይ መለስተኛ በሽታም ሊሆን ይችላል ወይም አደገኛ የእድሜ ልክ በሽታ ሊሆንም ይችላል።

ስር የሰደደ ሄፓታይተስ ቢ በሽታ ካለባቸው 4 ሰዎች 1 ሰው አደገኛ የጉበት ችግሮችን ያዳብራል፣ ካንሰርም ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ህክምና እና መቆጣጠር በመጀመሪያ ደረጃ መለያ ማድረግ ይቻላል።

## ሄፓታይተስ ቢ እንዴት ይተላለፋል?

ሄፓታይተስ ቢ ከሠው ወደ ሰው በደም ንክኪ ወይም በሰውነት ፈሳሾች ይተላለፋል። በሚከተሉት መንገዶች ሊተላለፍ ይችላል፡-

- በወሊድ ወቅት ከነፍሰ ጡር ሴት ወደ ልጅ
- ሄፓታይተስ ቢ ካለበት ሰው ጋር የደም ንክኪ ማድረግ
- የግል ንጽህና መጠበቂያ እቃዎችን እንደ የጥርስ ቡርሽ፣ ምላጭ፣ የጥፍር መቁረጫ፣ ወይም የህክምና ቁሳቁሶች (እንደ የግሉኮስ መቆጣጠሪያ) ያሉ የግል እንክብካቤ እቃዎችን ሄፓታይተስ ቢ ካለበት ሰው ጋር መጋራት
- ጾታዊ ግንኙነት
- መርፌዎችን፣ ሲሪንጆችን፣ ወይም የመድሃኒት ማዘጋጃ ቁሳቁሶችን መጋራት

## ሄፓታይተስ ቢ በሚከተሉት ነገሮች አይተላለፍም፡-

- ምግብን ወይም የመመገቢያ እቃዎችን በመጋራት
- እንደ መተቃቀፍ፣ መሳሳም፣ ወይም እጅ መያዝ ያሉ የተለመዱ ንክኪዎች
- ውሃ ወይም አየር

## ለበለጠ መረጃ፡-

**Centers for Disease Control and Prevention (CDC፣ የበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማዕከላት)**
www.cdc.gov/hepatitis/hbv/

HepBHub
doh.wa.gov/hepbhub

DOH 420-405 May 2022 Amharic

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ በ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም የመስማት እክል ያለባቸው ደንበኞች፣ እባክዎ 711 (Washington Relay) ላይ ይደውሉ ወይም በ civil.rights@doh.wa.gov ኢሜይል ያድርጉ።

ምንጭ፡- Minnesota Department of Health, Hepatitis B



# ሄፓታይተስ ቢ፡-

## ሁሉም ሰው ማወቅ ያለበት

Washington State Department of Health




## መመርመር ያለበት ማን ነው?

ሄፓታይተስ ቢ እንዳለብዎት ማወቂያ ብቸኛው መንገድ መመርመር ነው።

- ሁሉም ነፍሰ ጡር ሴቶች በየጊዜው ለሄፓታይተስ ቢ መመርመር አለባቸው። ነፍሰጡር ሴት ሄፓታይተስ ቢ ካለባት፣ በጊዜው መከተብ ቫይረሱ ወደ ልጁ እንዳይተላለፍ እንዲያደርግ ይረዳል።
- ሄፓታይተስ ቢ ካለበት ሰው ጋር የሚኖሩ ሰዎች።
- ከፍተኛ የሄፓታይተስ ቢ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች፣ ይህን ያካትታል፦
    - ሄፓታይተስ ቢ በጣም የተለመደባቸው እንደ አፍሪካ ወይም እስያ ወይም ወላጆቻቸው በእነዚህ ቦታዎች የተወለዱ ሰዎች
    - እጽ የሚወስዱ ሰዎች
    - ከወንድ ጋር ጾታዊ ግንኙነት የሚያድርጉ ወንዶች

## መከተብ ያለበት ማን ነው?

Centers for Disease Control and Prevention (CDC፣ የበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማዕከላት) ለብዙ ሰዎች የሚከተሉትንም ጨምሮ የሄፓታይተስ ቢ ክትባት እንዲያገኙ ይመክራል።

- ሁሉም ጨቅላ ህጻናት
- መንስኤዎቹ ምንም ይሁኑ ምን፣ ሁሉም ያልተከተቡ ልጆች እና እድሜያቸው እስከ 59 የሆኑ አዋቂዎች
- 60 አመታቸው እና ከዚያ በላይ የሆኑ አዋቂዎች፦
    - በጾታዊ መጋለጥ ምክንያት የኢንፌክሽን ስጋት ላይ ያሉ ሰዎች
    - በፐርኪውታኒየስ ወይም ሙኮሳል የደም ተጋላጭነት ኢንፌክሽን ስጋት ላይ ያሉ ሰዎች
    - መካከለኛ ወይም ከፍተኛ የሄፓታይተስ ቢ ኢንፌክሽን ያለባቸው አካባቢዎች የሚጓዙ ተጓዦች
    - ስር የሰደደ የጉበት በሽታ ያለባቸው ሰዎች
    - የኤች አይ ቪ ኢንፌክሽን ያለባቸው ሰዎች
    - የታሰሩ ሰዎች
    - የሄፓታይተስ ቢ መከላከያ የሚፈልጉ ሌሎች ሁሉም ሰዎች



**በአለም አቀፍ ደረጃ በግምት እስከ 296 ሚሊዮን ሰዎች ከሄፓታይተስ ቢ ጋር እየኖሩ ነው፣ ነገር ግን አብዛኞቹ ይህን አያውቁም ምክንያቱም ህመም አይሰማቸውም ወይም የታመሙ አይመስሉም።**



## ክትባቱ አስተማማኝ ነው?

የሄፓታይተስ ቢ ክትባት አስተማማኝ እና ውጤታማ ነው። በU.S ከ1982 ጀምሮ ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል።

ከአንድ ቢሊዮን በላይ የሄፕታይተስ ቢ ዶዞች በለም አቀፍ ደረጃ ተሰጥተዋል።

የክትባቱ በጣም የተለመዱ ምላሾች ክትባቱ በተሰጠበት ላይ ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ ትኩሳት መኖር ነው። እነዚህ የጎንዮሽ ጉዳቶች ከ 1-2 ቀናት ይቆያሉ።

## የሄፓታይተስ ቢ ክትባቱን የት ማግኘት እችላለሁ?

ክትባት ስለማግኘት ፋርማሲዎን፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን፣ ወይም የአካባቢ ጤና መምሪያን ያነጋግሩ። አንዳንድ ክሊኒኮች በነጻ ወይም በዝቅተኛ ክፍያ የሄፓታይተስ ክትባት ይሰጣሉ።

የጤና ኢንሹራንሶች ክትባቱን እድሜያቸው እስከ 59 አመት ለሆናቸው እና ከተጋላጭ የሆኑ እና ከ60 በላይ ለሆናቸው ለሁሉም ሰዎች የክትባት ሽፋን ያደርጋሉ።

ከወለዱ፣ ከመልቀቅዎ በፊት በሆስፒታሉ ውስጥ ልጅዎ የሄፓታይተስ ቢ ክትባቱን ማግኘት ይችላል። ክትባቱ አዲስ ለተወለዱ ልጆች በነጻ ይሰጣል።